በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA MINISTRY OF FOREIGN AFFAIRS

ፕሬስ መግለጫ PRESSRELASE

# የአሰብ ወደበን ስራ ለማስቀጠል ዝግጅት ተጀመረ

የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ በኤርትራ ጉብኝት ማድረጋቸውን ተከትሎ የተፈረመው የሠላምና የወዳጅነት የጋራ መግለጫ በተፋጠነ ሁኔታ እየተፈፀመ መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አቶ መለስ ዓለም ገልጸዋል፡፡

አቶ መለስ ዛሬ በሰጡት መገለጫ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ አስመራ ከሁለት አስርት ዓመታት በኃላ የመጀመሪያውን በረራ በነገው ዕለት ሐምሌ 11/2010 ዓ.ም እንደሚካሄድ፤ 465 ተጓዦች ወደ አስመራ ጉዞ እንደሚሄድ አስታውቀዋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ አስመራ መብረር ሲጀመር ኤርትራ ከ115 ዓለም አቀፍ የመዳረሻ ጣቢያዎች ጋር ትገናኛለች፤ ምቹ የአየር ግንኙነት መፈጠሩም ለሁለቱም ሀገሮች ኢንቨስተሮችን ለመሳብ እና የቱርስቶች ፍሰት እንዲጨምር ያደርጋል ሲሉ አቶ መለስ በመግለጫቸው ተናግረዋል።

የአሰብ ወደብ አገልግሎት በአፋጣኝ የሚጀመሩበት ሁኔታ እንዲመቻች የሁለቱ አገራት መሪዎች መመሪያ መስጠታቸውን እና በዚህም መሰረት የትራንስፖርት ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ የማሪታይም አገልግሎት ባለስልጣን እና የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት ሎጂስቲክ አገሎግሎት ድርጅት እና ሌሎች አካላት ያሉበት ግብረሀይል ተቋቁሞ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን አቶ መለስ በመግለጫቸው ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ እና ኤርትራ የድንበር አከባቢዎች በተለይም በትግራይና አፋር ክልሎች የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት እንዲኖር ሁለቱም አገሮች እየሰሩ እንድሚገኙም ተገልጿል፡፡

ከኮምኒኬሽን አንፃር በሁለቱ ሀገራት ተቋርጦ የነበረው የስልክ አገልግሎት ተጀምሯል፤ የተቋረጠውን ዝምድና መጠገን ተችሏል የልዩነት ግንብ ፈርሶ የወዳጅነት ድልድይ ተሰርቷል፤ ሁለቱም አንድ ህዝቦች ሆነዋል ብለዋል፡፡

E-mail spokesperson@mfa.gov.et facebook @mfaEthspokesperson, Twitter @mfaEthspokesperson,
YouTube https://www.youtube.com/channel/UCa_KUDpwCLMWyyQIjfilgZg ☎ 011-5-15 8928/011-5-53 6731 Fax 011-5-51-43-00
✉393 Addis Ababa,Ethiopia

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA MINISTRY OF FOREIGN AFFAIRS

ፕሬስ መግለጫ PRESSRELASE

በዲፕሎማሲው በኩል ግንኙነቱን ቀድሞ ወደ ነበረበት የመመለስ (Normalization) አስመልክቶ የኤርትራ ኤምባሲ አዲስ አበባ ውስጥ ተከፍቷል፤ የኢትዮጵያ ኤምባሲም አስመራ ለመክፈት እየተሰራ መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ገለፀዋል፡፡

በኢትዮጵያ እና ኤርትራ መሀል ከሁለት አስርት አመታት በላይ ያስቆጠረ የዕልቂት እና የፅልመት ታሪክ ለመለወጥ በመሪዎቻችን በኩል ድፍረት የተሞላበት ቁርጠኛ ውሳኔ በማሳለፋቸው ዓለም አድናቆቱን እየገለፀ መሆኑን አቶ መለስ በመግለጫቸው ተናግረዋል።

**የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር**

**ቃል አቀባይ ጽ/ቤት**

**ሐምሌ 10 ቀን 2010 ዓ.ም.**

E-mail spokesperson@mfa.gov.et facebook @mfaEthspokesperson, Twitter @mfaEthspokesperson,
YouTube https://www.youtube.com/channel/UCa_KUDpwCLMWyyQIjfilgZg ☎ 011-5-15 8928/011-5-53 6731 Fax 011-5-51-43-00
✉393 Addis Ababa,Ethiopia